‹‹በሰሜን እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን ህገወጥ ስደት ማስቆም - ሲንስ››

## ሲንስ ሙዚቃ

## ክፍት የውድድር ደንቦች

1. **መግቢያ**

   ሲንስ በአዲስ አበባ በጣሊያን ኤምባሲ የሚተዳደር እና በአውሮፓ ህብረት ለአፍሪካ የባለ አደራ ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ፕሮግራም ነው፡፡ የሲንስ አላማ በኢትዮጵያ ለስደት ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች፣ ሴቶችና፣ ከስደት ተመላሰሽ ለሆኑ ምቹ የስራ ቅጥር እድሎችን በማሳደግ በሰሜን እና ማእከላዊ ኢትዮጵያ እየተስተዋለ ባለው ህገ-ወጥ ስደት ምክንያት የሚፈጠረውን ተጽእኖ መቀነስ ነው፡፡

   የውድድሩ አላማ

   በህገ-ወጥ ስደት ምክንያት ስለሚፈጠሩ ስጋቶች ግንዛቤን ለማስጨበጥ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ምቹ የስራ እድሎችን ለመፍጠር ሲንስ የሀገር ውስጥ አርቲስቶችና መላውን ህብረተሰብ የሚያሳትፍ የሙዚቃ ውድድር አዘጋጅቷል፡፡

2. **ሽልማት**

   ለሙዚቃ ውድድር አሸናፊው የኢት ብር 30,000 ይሰጠዋል እንዲሁም ሙዚቃውን አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ ፕሮፌሽናል የሙዚቃ ስቱዲዮ ውስጥ የሚያስቀርጽበት እድል ይሰጠዋል፡፡ ከዚያም ሙዚቃው በሀገር አቀፍ ደረጃ በሀገር ውስጥ የራዲዮ ጣቢያዎች እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡

   አሸናፊው በተጨማሪም በአዲስ አበባ በሰኔ 2011 ዓ.ም በሚዘጋጀው ከሲንስ ፕሮግራም ጋር ተያያዥነት ባለው ዝግጅት ላይ ይሳተፋል፡፡

3. **ተደራሽ የሚሆኑ አድማጮች/ታዳሚዎች**

   የሚቀርቡት ሙዚቃዎች ትኩረታቸውን በስደተኞች በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ሙዚቃዎቹ በተገቢ የማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ ዝግጅቶች እና የሲንስ ፕሮግራም ስብሰባዎች ላይ እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

4. **ማመልከቻ**

የማመልከቻ ማቅረቢያ የመጨረሻ የመዝጊያ ቀን አርብ ግንቦት 23/2011ዓ.ም በምስራቅ አፍሪካ ሰአት አቆጣጠር 17:00ሰዓት (11:00ሰዓት) ድረስ መቅረብ አለባቸው። ማመልከቻዎች አዲስ አበባ በሚገኘው የጣሊያን ኤምባሲ ‹‹የሲንስ ፕሮግራም ጽ/ቤት›› በአካል ሊቀርቡ ወይም በኢሜይል addisababa.since@esteri.it ሊላኩ የሚችሉ ሲሆን የሚከተሉት ሰነዶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡

ሀ) በአግባቡ የተሞላና የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ (አባሪ 1ን ይመልከቱ)

ለ) የሙዚቃው ኤምፒ3 ፎርማት በሲዲ (ወይም በአማራጭነት በዌትራንስፈር፣ ዩሴንድ ኢት ወይም ድሮፕ ቦክስ ላይ መጫን እና ከላይ በተገለጸው የኢሜይል አድራሻ መላክ ይችላል)

ሐ) የሙዚቃውን ይዘት (ግጥም) በጽሁፍ

መ) ህጋዊ መታወቂ ወይም ፓስፖርት ኮፒ

5. **የብቁነት መስፈርት**

**ጭብጥ**

በአጠቃላይ የሲንስ የሙዚቃ ውድድር አላማ ህገ-ወጥ ወይም ኢ-መደበኛ ስደት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ባርነት፣ የጾታዊ ጥቃት፣ የጉልበት ብዝበዛ እና ጥቃቶችን ከምንጩ ለማስቀረት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ምቹ የስራ እድሎች መፍጠር የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ላይ ያተኮሩ መሆን አለባቸዉ።

**የአቀራረብ/ዘይቤ**

ተወዳዳሪዎች የሙዚቃውን አቀራረብ/ዘይቤ በነጻነት መምረጥ ይችላሉ (በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች መካከል የሚደረግ ምልልስ(ዲያሎግ)፣ ውይይት፣ ታሪክ መተረክ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል)። የሙዚቃው አቀራረብ ለአዲሱ ትውልድና ወጣቶች ሳቢነት ያለው መሆን አለበት።

**ደራሲ (ዎች)**

የሚቀርቡት ሙዚቃዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ደራሲ ሊኖራቸው ይችላል። ተሳታፊዎቹ የሙዚቃው ደራሲዎችና የስራቸው የቅጂ መብት ባለቤቶች መሆን አለባቸው። አንድ ደራሲ ወይም የደራሲዎች ቡድን ከሁለት ሙዚቃዎች በላይ ማቅረብ አይችሉም።

**ይዘት**

የግምገማ ኮሚቴው የትኛውንም ጎጂነት ያለው፣ አሳሳች የሆነ፣ ስም የሚያጎድፍ ወይም አጸያፊ ይዘት ያለው ወይም የትኛውንም እንደ ወንጀል ጥፋት የሚቆጠር ወይም የወንጀል ድርጊት የሚያበረታታ፣ ከማህበረሰቡ ባህል እና እሴት ጋር የሚቃረን፣ የትኛውንም ሀገራዊ ወይም አለም አቀፍ ህግ የሚጥስ ይዘት ያለው ሙዚቃ ከውድድሩ የማስወጣት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የቋንቋ መስፈርቶች**

የሙዚቃው ይዘት ጽሁፍ በአማርኛ ቋንቋ መዘጋጀት አለበት፡፡

**ርዝመት**

የሙዚቃው ርዝመት ቢበዛ ከ180 ሰከንዶች መብለጥ የለበትም፡፡

**ፎርማት**

ሙዚቃው በኤምፒ3 ፎርማት ከሙዚቃው ይዘት ጽሁፍ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት፡፡

**የሌለውን ስራ የራስ አድርጎ መጠቀም**

የሌላ ደራሲ ጽሁፍ ወይም ሙዚቃን እንደ እራስ አድርጎ መጠቀም ወይም ማቅረብን ከውድድሩ ማስወጣትን ያስከትላል፡፡ ቆይቶ የሚታወቅ የሰው ስራ የራስ አስመስሎ መጠቀም አሸናፊዎች አሸናፊነታቸው እንዲነጠቅ ያደርጋል፡፡

6. **የምርጫ ሂደት**

**የግምገማ መስፈርቶች**

ሙዚቃዎቹ በሚከተሉት በቅድሚያ የተዘጋጁ መስፈርቶች (በውጤት ደረጃ ከ0 እስከ 5) መሰረት ይገመገማሉ፡-

- **ለሲንስ ፕሮግራም አላማዎች ተገቢነት፡** ሙዚቃዎቹ ህገ-ወጥ ስደት የሚያስከትላቸውን ችግሮች እና በኢትዮጵያ ውስጥ የስራ እድሎችን መፍጠር የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች የሚገልጹ መሆን አለባቸው፡፡
- **ግጥም፡** የቃላት አጠቃቀም ብልህነት፣ ፈጠራና የማሰብ ችሎታን ይመዝናል፡፡

- **ዜማ፡** የሁሉም ሙዚቃዎች የድምጽና ዜማ ፍሰት ልዩነት ይፈጥራል። ዳኞች የዜማውን ቀጣይነትና ህብር እንዲሁም የድምጽ አወጣጥ፣ ንዝረትና ስታይልን ይመዝናሉ።
- **ሳቢነት፡** ሙዚቃው ለአብዛኛው አድማጭ ሳቢነት ያለው ነው? የሙዚቃው የሲንስ ፕሮግራም ካበቃ በኋላ በራዲዮ የመሰራጨት እድል ምን ያህል ነው?

ለሲንስ ፕሮግራም አላማዎች ተገቢነት ዋነኛው መስፈርት ሲሆን በዚህ ዜሮ ውጤት ማምጣት ተወዳዳሪው ከውድድሩ እንዲወጣ ያደርጋል።

**ቅድመ ምርጫ**

ሙዚቃዎቹ በጣሊያን ኤምባሲ ከሀገር ውስጥ የሙዚቃ ሙያተኞች ጋር በትብብር የቅድመ ምርጫ ዙር ይካሄድባቸዋል።

በቅድመ ምርጫ ግምገማ ምክንያት አማካኝ ውጤት 10/20 ውጤት ያመጣ ምንም ሙዚቃ የማይኖር ከሆነ የጣሊያን ኤምባሲ ምንም የተሳትፎ ወይም በተሳታፊዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ክፍያ መክፈል ሳይጠበቅበት ሁሉንም የውድድር ሂደት የመሰረዝ/የማቋረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ምርጫ**

ከዚያም ቢበዛ አምስት የተመረጡ ተወዳዳሪዎች ወጣቶችና የልማት ተሳታፊዎችን በሚይዝ ገለልተኛ ዳኛ ዳኝነት ይሰጥባቸዋል።

የውድድሩ አሸናፊዎች በሰኔ 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ በሚዘጋጀው የማህበረሰብ ዝግጅት ላይ የሚገለጹና ሽልማት የሚሰጣቸው ይሆናል። የዳኛ ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል።

7. **የቅጂ መብት**

አዲስ አበባ የሚገኘው የጣሊያን ኤምባሲና የገንዘብ ድጋፍ ሰጪው (የአውሮፓ ህብረት) በአሸናፊው ሙዚቃ ላይ የባለቤትነት መብት የመጠየቅ እና ሙዚቃውን ከሲንስ ፕሮግራሞች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ዝግጅቶች ላይ፣ በራዲዮ፣ የኢንተርኔት ድረገጽ እና ከፕሮግራሙ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የማሰራጨት መብት አላቸው።

**ANNEX 1 - ቅጥያ 1**

**SINCE SONG Application Form - የሲንስ ሙዚቃ አመልካች ቅጽ**

| | |
|---|---|
| **Song Title***<br>**የሙዚቃው ርዕስ*** | |
| **Lead applicant Name & Surname***:<br>**የዋና አመልካች ሙሉ ስም እስከ አያት*፡** | |
| Co-applicant 1 Name & Surname:<br>የረዳት አመልካች 1 ሙሉ ስም እስከ አያት፡ | |
| Co-applicant 2 Name & Surname:<br>የረዳት አመልካች 2 ሙሉ ስም እስከ አያት፡ | |
| o-applicant 3 Name & Surname:<br>የረዳት አመልካች 3 ሙሉ ስም እስከ አያት፡ | |
| Co-applicant 4 Name & Surname[1]:<br>የረዳት አመልካች 4 ሙሉ ስም እስከ አያት፡ | |
| **Lead applicant Telephone***<br>**የዋና አመልካች ስልክ ቁጥር*፡** | |
| **Lead applicant Email Address***<br>**የዋና አመልካች የኢሜይል አድራሻ*፡** | |

[1] If more than 4 co-applicants please attached a document with full information (name and surname).
ከ4 በላይ ረዳት አመልካቾች የሚኖሩ ከሆነ እባክዎ ከተሟላ መረጃ ጋር ከዚህ ሰነድ ጋር አያይዘው ያቅርቡ (ስም እስከ አያት)

**Lead applicant ID No/Passport[2]***
**የዋና አመልካች መታ/ቁ/ፓስፖርት ቁ.2*:**

| |
|---|
| |

**Statement of Consent - የፍቃድ መግለጫ**

I hereby give my consent to the SINCE PROGRAMME, its affiliates and agents, to use the song or parts of the song for all relevant purposes to the Programme (including utilization in awareness campaigns, broadcasting on radio, television and electronic media, including internet).

**ለሲንስ ፕሮግራም፣ ተባባሪዎቹና ወኪሎቹ ሙዚቃዬን ወይም የሙዚቃዬን ከፊል ክፍል ለሁሉም የፕሮግራሙ ተገቢ አላማዎች እንዲጠቀሙበት (ለግንዛቤ ፈጠራ ዘመቻዎች መጠቀምን፣ ኢንተርኔትን ጨምሮ በራዲዮ፣ ቴሌቭዥንና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማሰራጨትን ጨምሮ) የፈቀድኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።**

Date - ቀን : ______________________

Lead applicant signature: **የዋና አመልካች ፊርማ:**______________________________

[2] Please attach a copy of the lead applicant identification document (ID) or passport.
እባክዎ የዋና አመልካች መለያ ሰነድ (መታወቂያ) ወይም ፓስፖርት ኮፒ ያያይዙ ::